በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 2

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon3@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

**ሚያዝያ ፮ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም.**

# ጋብቻ

## *ባለፈው ሳምንት*


1. በ1ኛ ዮሐ 1፡1 "ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን::" እንደ ተጠቀሰው ከጌታችን በማየት፣ በመስማትና በመማር ዘወትር ማፍቀር እንዳለብን
2. በኤፌ 5፡32 እንደ ተገለጸው ጋብቻ ታላቅ ምስጢር መሆኑን
3. ለቅዱስ ቁርባን ስለ ሚያስፈልገው ዝግጅት በ1ኛ ቆሮ 11 የተጻፈልንን ምሳሌ አድርገን ለጋብቻ ዝግጅት እንደያሚሻውና ከማግባትም በፊት ስለ ቅዱስ ጋብቻ በአግባብ መረዳታችንን ማረጋገጥ እንደሚኖርብን
4. ቅዱስ ጎርጎርዮስ ጋብቻ መስጠትና መሥዋዕትነት እንደሆነ ከመግለጽ ጋር ጌታችን ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደዳት ባሎች ሚስቶቻቸውን መውደድ እንደሚገባቸው ሚስቶችም ቤተ ክርስቲያንን ለክርስቶስ እንደምትታዘዘው ለባሎች መታዘዝ እንዳለባቸው የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት ተርጉሞ ማስረዳቱን
5. እስከ መተጫጨት ከጌታችን ጋር ጽኑ ወዳጅነት ማድረግ እንዳለብን፣ ከትዳር አጋር አንዱ ወደ ወዲያኛው ዓለም ቢጠራ እንኳ ከጌታችን ጋር ያለን ወዳጅነት ሳይበጠስ ተጽናንተን መቀጠል እንደሚያስችለን
6. ተጋቢዎች በጋብቻቸው ዕለት የመጀመሪያ ልጅ ጋብቻን እንደሚወልዱና ያ ልጅም በስሜት፣ በመንፈስ፣ በጥበብ፣ በአካል ማደግ እንደሚገባው፣ እንክብካቤና ማስታመምን እንደሚሻ
7. የእግዚአብሔር ቃል ጋብቻን ባለሥልጣን ሆኖ እንደሚመራው በዚህም መሠረት መተው፣ አንድ መሆንና መረዳዳት እንደሚኖር ተምረናል።

# ኅሊና፣ የእምነት ሥርዓትና የተደበላለቀ ጋብቻ

- ኅሊና መንፈስቅዱስ አይደለም፡፡ ***ዮሐ 17፡3*** የክርስቲያኖችን ዘላለማዊነት የሚያመለክት ሲሆን ከወላጆቻችን፣ ከአካባቢያችን የምንመለከተውን ተከትሎ ከ15 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ ያድጋል ይበለጽጋል፡፡ ከ18 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ በጎ/ክፉውን ማስገባት/ማውጣት እንችላለን፡፡
- የክርስቲያን ማንነት በተለያዩ መዋቅሮች ሲገለጽ
  - "የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ።" ***ቀዳ ተሰ 5፡23፡፡***

1. የሰው አካል፡ የተለያዩ ሕዋሳት የሚገኙበት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው፡፡
2. የሰው መንፈስ፡ መንፈስቅዱስ አይደለም፡፡
   - መገኛው መንፈስቅዱስ ነው፡፡
   - የሥነ ሕይወት ተመራማሪዎች ሊፈጥሩት የማይችሉት የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው፡፡ አዳምን ሕይወት ያለው ያደረገው እግዚአብሔር ነው፡፡ ***ዘፍጥ 2፡7፡፡***
3. የሰው ነፍስ
   - ጠንቅቀን የማናውቀው ስሜታችንን ወይም ድርጊታችንን የሚቆጣጠር ለብዎ፣ ኅሊና፣ ፈቃድ፣ መሻት (ሐሳብ)፣ ስሜት
4. መንፈስ ቅዱስ "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?" ***ቀዳ ቆሮ 3፡16፡፡***

# ጋብቻ



መንፈስ ቅዱስ
የሰው አካል
የሰው መንፈስ
ጠንቅቀን የማናውቀው ስሜታችንን ወይም ድርጊታችንን የሚቆጣጠር ለብዎ
ኅሊና
ፈቃድ
አሳብ
ኃጢአት
ስሜት
መለኮታዊ ረድኤትና ቅዱስ ሜሮን
ሰይጣንና ጽኑ ፈተናዎቹ እንዲሁም አንባቢና ሌሎችም

# ጋብቻ

- ሥዕሉ እንደ ሽንኩርት ኮንሰንትሪክ ክብ ነው፡፡
- የመጀመሪያው ሽፋን አካል ነው፡፡ ሁለተኛው ለአካል ሕይወትን የሚሰጠው መንፈስ ነው፡፡ ቀጥሎ የሚገኘው ነፍስ ነው፡፡
- በጥልቁ የሚገኘው ስሜት ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው ሰባት መዋቅሮች አሉት፡፡
- ስምንተኛው በተጠመቁ ኦርቶዶክሳውያን የሚኖር መንፈስቅዱስ ነው፡፡ መንፈስቅዱስ፡-
    - የሰው ሁለንተናውን የሰይጣን ከሆነ ወጥመድ ይጠብቃል፡፡
    - ተጠምቀን ቅዱስ ሜሮኑን ስንቀባ ይቀድሰናል፡፡
    - ልጅነትን በጥምቀት መቀደስን በሜሮን ስናገኝ ወደ ዘላለማዊነት ያደርሰናል፡፡
    - ክርስቲያኖች ያልሆኑ መንፈስቅዱስ ስለማይኖርባቸው ውስጣቸው ባዶ ወይም ቀፎ ነው፡፡
- ሁሉንም መዋቅሮች ከመንፈስቅዱስ የሚለያቸው በሥዕሉ የሚታየው ጥቁሩ ክብ ነው፡፡ እርሱም ኃጢአት ሲሆን ብንበድልም በንስሐ የመመለስም ዕድል ተሰጥቶናል፡፡
- መላ ነገራችን በመንፈስቅዱስ እርስ በርሱ ከተገናኘ የአምላካችን የመድኃኔዓለም መዓዛ ይኖረናል፡፡
- አንድ ጠርሙስ ሽቱ ምን ያህል ውድ ነው? መላ ሰውነታችን እንደ ሽቱ ይሆናል፡፡
- ኃጢአት በአንዱ ክፍል ውስጥ ከተገኘ መጥፎ ጠረን ይኖረናል፡፡
- ከጌታችን ጋር የምንኖር ከሆንን እንደ ሽቱ የሆነ መዓዛ ይኖረናል በዚህም የተነሳ የእግዚአብሔር ሰው ሐሳባችንን፣ ድካማችንን፣ ጥረታችንን፣ መውጣት መውረዳችንን … ያደንቅልናል፡፡ የክ

# ጋብቻ

- በቤተ ክርስቲያን ምሰሶ የምናገኘውን የመስታወት/ክሪስታል እንውሰድ፡፡ ክሪስታሉ/መስታወቱ ጥርት ያለ ንጹሕ ነው፡፡ በጥምቀት የሚታደሰው ሰውነታችንም እንዲሁ ነው፡፡

- ጤናማ ዓይን ያለው ሁሉ በእኛ ውስጥ የሚገኘውን መንፈስቅዱስ መመልከት ይችላል፡፡
- 
- በክሪስታሉ ላይ ጭቃ ከቀባን ብርሃኑን ማየት አንችልም፡፡ እኛ ስላልታየን ክሪስታል መሆኑ ቀረ ወይም ተለወጠ ማለት ግን አይደለም፡፡
- ጭቃ የክሪስታሉን ውስጣዊ አካል ወይም የተሰራበትን ንጥረ ነገር ጠልቆ ሊገባ አይችልም፡፡ ጭቃውም ኃጢአት ነው፡፡
- ኃጢአት አዲሱን ተፈጥሮአችንን ጠልቆ ገብቶ አይደመስሰውም፡፡ የሚያቆሽሰው የሚቻለውን የሚደርስበትን ነው፡፡
- ክሪስታሉን ለማጽዳት እናጥበዋለን፡፡ እንዲሁ ወደ ንስሐ አባታችን በመሄድ በንሥሐ በመታጠብ ራሳችንን ከኃጢአት ንጹሕ ማድረግ ይኖርብናል፡፡

- በንስሐ ከተመለስን የማይደመሰስ ኃጢአት የለም፡፡
- በብርሃንና በጨለማ መካከል ምንም ኅብረት የለም፤ ይህን ግልጽ እውነታ በመረዳት ከጨለማ በመራቅ በብርሃን መመላለስና ብርሃንን መለበስ ያስፈልገናል፡፡

# ጋብቻ

- **እግዚአብሔር ለእኛ ማነው? በውስጣችን እንዴት እንስለዋለን? መድኃኒታችን፣ ሕይወታችን፣ አምላካችን፣ አባታችን … ነው፡፡**
- "ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል። ወይስ ከእናንተ፥ ልጁ እንጀራ ቢለምነው፥ ድንጋይን የሚሰጠው ከእናንተ ማን ሰው ነው? ዓሣስ ቢለምነው እባብን ይሰጠዋልን? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን አይሰጣቸው? " … **ያለን ምን ያህል የፍቅር አምላክ እንደሆነ ለማስገንዘብ ነው፡፡** ***ማቴ 7፡7-9፡፡***

- **ድምጹን ባልሰማን ጊዜ ለኢየሩሳሌም ለአይሁድም እንዳለቀሰ ያለቅሳል፣** "በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም። የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም። እኔና አብ አንድ ነን። አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ።" ***ዮሐ 10፡27-31፡፡***
- **በገዛ ፈቃዳችን እስካልተውነው ድረስ አይተወንም፡፡ በሮችዋ የተከፈቱ ቤተ ክርስቲያናችን ይህች ናት፡፡ የምታስተምረንም ይህንን ነው፡፡ በሮችዋን ከፍታ ወደ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሕይወት እንድንቀርብ ትጋብዘናለች፡፡**
- **ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ምስጢረ ሥላሴ፣ ነገረ ድኅነት፣ ምሥጢረ ሥጋዌ፣ ዘላለማዊ ፍርድ፣ አማላጅነት፣ ቤተ ክርስቲያን… የምታስተምረውን አስቀድሞ መረዳት ለሁሉም ተገቢ ነው፡፡**

# ጋብቻ

*ከጋብቻ አስቀድሞ፡-*

- ከዓለም ልጆች የተለየንና በሳል ኅሊና ያለን መሆናችንን በመመርመር ሰይጣን በሰለጠነ መንገድ የሚያስትበትን ጎዳና የተረዳን መሆን ይገባናል፡፡ ሰይጣንም የሚያስትባቸውን ዘዴዎች ቢያንስ በሚከተሉት መንገዶች ይገልጣቸዋል
    - የእግዚአብሔርን የቃሉን ሥልጣን በማቃለል
    - ራሳቸውን በሚቆጣጠሩ የተከበሩ ጎልማሶች እስከተፈጸመ ድረስ ወሲባዊ ግኑኝነት ነውርነት የለውም የሚሉ ወገኖችን በማደፋፈር
    - ልቅ የወሲብ ግኑኝነት ፊልሞች፡- የልጆችን ሕይወት መበዝበዝ፣ የሴቶችን ጉዳትና የቤተሰብን መበተን እንዲያስከተሉ በማድረግ፣
    - ሰዎችን ለማስደሰት የምንሄድባቸው ከሞራል ውጪ የሆኑ መንገዶች፣ በሃይማኖት አለመጽናት፣ በሥጋ የሚገኝ ደስታን እንደ መሠረታዊ ነገር መቁጠር፣ የእግዚአብሔርን እርዳታ እንዳንፈልግ የሚያደርጉ እንዲሁም ትሑት መሆንን የሚያጣጥሉ አካሄዶች በማለማመድ፣
    - መንፈሳዊ እውነታዎችን በአእምሮ ኃይል፣ በምትሐት፣ በልምድ ብቻ ለማግኘት እንድንጣጣር በማድረግ
    - ፓንቴይዝም "እንደ እግዚአብሔር ነህ" ዘፍጥ 3፡4፣ "ሁሉም እግዚአብሔር ነው እግዚአብሔርም ሁሉንም ነው" በሚሉ ዘመነኞች ከሃድያን እንድንማረክ በማድረግ፤
    - ተመልሶ በሌላ አካል ዳግመኛ ተወልዶ ወደዚህ ዓለም መምጣት አለ ብለን እንድናምን በማድረግ፣
    - "ላንተ መልካም የሆነ ለእኔ ላይሆን ይችላል፣ በዚህ ዓለም ፍጹም እውነት የለም መልካምና ክፉ ጓደኞች ናቸው" ብሎ በማሳመን፡፡
    - "መዳን በልልምድ በሚደረግ ተመስጦ (Transcendental Meditation) ይገኛል፣ በልልምድ የሚደረግ ተመስጦም ዓይንን ይገልጣል" እያለ  በማሳመን… ወዘተ

-

# የተደበላለቀ ጋብቻ

- ጋብቻ መደበላለቁ የሚታወቀው፡-
    - በተለያየ ባህል፡ - ቋንቋ፡ አመጋገብ፡...፣
    - በተለያየ ሃይማኖት፣
    - በተለያዩ ቡድን ... የተነሳ ይሆናል፣
    - ያለመግባባት ምንጭ በመሆኑ፣
    - ውጤቱ መልካም ባለመሆኑ፣

***<u>የእምነት መዋቅሮቻችንና የተደበላለቀ ጋብቻን ራሱ ማጣጣም እንዴት ይቻላል?</u>***

- **የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን፡- የቀናች፣ ሐዋርያዊት፣ ትውፊታዊት፣ የራስዋ ቅዳሴ ያላት፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊት፣ ገዳማዊት፣ በምስጢራት በአግባብ የምትጠቀም ክርስቲያን፣ ኢትዮጵያዊት፣ የተዋበች መንፈሳዊት ቤተ ክርስቲያን መሆንዋን ከጋብቻ አስቀድሞ በአግባብ በመረዳት**
- **ቤተ ክርስቲያናችን ለሁሉም ነገድ፣ ጎሳ፣ ዜጋ ቤተክርስቲያኒቱን ያውቃት ዘንድ በርዋ የተከፈተ ሁሉንም በደስታ ተቀብላ የምታስተናግድ የምታኖር መሆንዋን በማወቅ፤**
- **ሁሉም ቀርበው የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርት፣ ትውፊት፣ ሃይማኖትና ሥርዓት አውቀው አምነው ሊከተሉዋት የሚችሉበት በር ክፍት እንደሆነ በማስተዋል፣**

- **ሁላችንም በቤተ ክርስቲያናችን ስለኖርን ቅዳሴውን፣ ሰዓታቱን፣ ማኅሌቱን ስንሰማ ያስደስተናል፡፡ የሚያስደስተን ቤተ ክርስቲያናችን ኢትዮጵያዊም ስላላበሰችው ጭምር ነው፡፡**

# ለተደበላለቀ ጋብቻ መፍትሔዎች

- ማንም ወደ ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ሊገባ ቢሻ የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት፣ የመረጣቸውም የወዳጆቹ ምንነት፣ ሥርዓትዋ… ትምህርት በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮ ሊገለጥለትና ሊያምን ይገባል፡፡ ይህም ጋብቻ ስለሚመሠርት ብቻ መሆን የለበትም፡፡

- የቤተ ክርስቲያናችን ድንበርዋ አድማስ ነው፡፡ በየትኛው ክፍለ አህጉር አለች፡፡ በአፍሪካ፣ እስያ፣ አውስትራሊያ፣ ሰሜን አሜሪካ፣ ደቡብ አሜሪካ ውስጥ ትገኛለች፡፡

- በሌላ ቤት ቆይቶ ወደ ቤተክርስቲያናችን የሚመጡ የሚገጥማቸው ይኖራል፡፡ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴው ሦስት ሰዓት ይወስዳል፣ በካቶሊኮች አንድ ሰዓት ነው፡፡ ዲያቆን መባል ለሌሎች ቀላል ነው በቤተ ክርስቲያናችን ግን ሥርዓት ያለው ኀዳና አለ… ይህ በውጪ ሆነው የተለያየ ነገር ለለመዱ ቀላል ኤአደለም፡፡ ከመጡ ግን የቤተ ክርስቲያኒቱን ተቀብለው መኖር ይጠበቃል፡፡

- በዚህ ክፍለ ዘመን ያለ ፈተናን ተቋቁሞ ሌሎችን መታደግ ግን ከሁሉ ይጠበቃል፡፡

**ሁላችንንም ራሳችንንም ሆነ ሌላውን ለማነጽ የበቃን ያድርገን፡፡ አሜን!!!**

... ክፍል ሦስት

“የሕይወት አጋርን መምረጥ”

ይቀጥላል፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡